ጉባዔ ዐሥራ ሁለት።

ይኸ..

ይበል ካህን።

ጸሎተ ፈትሖ።

ቁሱ ኅብስቱን በፈተተ ጊዜ ሲፈትት የሚጸልየው ጸሎት ይህ ነው፤ ዲያቆኑ ሦስት አኰቴት አምጥቶ ይሰጠዋል ያላረረውን ያልጠቆረውን ነቅ የሌለበትን አንዱን ለይቶ አስቀርቶ ሁለቱን እዛው በመሶበ ወርቅ እንዳሉ ይመልሳቸዋል፤ ይኸውም ምሳሌ ነው፤ ሦስቱ አኰቴት የሦስቱ አካላት ካህኑ ለይቶ ያነሣው የወልድ ምሳሌ ነው በተለየ አካሉ ሰው ሆኖ መሥዋዕት ሆኗልና፤ ሁለቱ አኰቴት የአብና የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ወልድ ሰው ሲሆን እነሱ ሰው አልሆኑምና። አንድም ዮሴፍና ኒቆዲሞስ ጌታን ቀብረው የመመለሳቸው ምሳሌ፤ አንድም የፈያታዊ ዘየማንና የፈያታዊ ዘፀጋም ምሳሌ ጌታ ሲቀበር እነሱ አልተቀበሩምና። ገባሬ ሠናዩ ካህንና ንፍቁ ካህን ውስጥ ለውስጥ ይቀባበሉታል ከሐና ወደ ቀያፋ ከቀያፋ ወደ ሐና እያመላለሱ ጌታን አንገላተውታልና የዚያ ምሳሌ ነው። ወአመ ረፈቀ ውስተ ቤተ አልዓዛር ዓርኩ እምዘ አምጽኡ

ሎቱ ለድራር እንዲል[124] ከወዳጁ ከአልዓዛር ቤት ግብር አግብቶ ሳለ ለበረከት ካመጡለት ከኅብስቱ ከወይኑ ከፍሎ ዝ ውእቱ ሥጋየ ወዝ ውእቱ ደምየ ብሎ አክብሮ ለውጦ ትኩስ ሥጋ ትኩስ ደም አድርጎ ሰጣቸው፡፡ ይህን ከላይ ወደ ታች እየፈተተ ይወርዳል በደሙ ያትመዋል፤ ከላይ ወደታች፣ ከታች ወደ ላይ፣ ከቀኝ ወደ ግራ፣ ከግራ ወደ ቀኝ ይፈትተዋል፤ ከላይ ወደ ታች መፈተቱ የአምላክ ሰው መሆን፤ ከታች ወደ ላይ መፈተቱ የሰው አምላክ መሆን፤ ከቀኝ ወደ ግራ ከግራ ወደ ቀኝ መፈተቱ ከናዝሬት ወደ ገሊላ ከገሊላ ወደ ናዝሬት ተመላልሶ የማስተማሩ ምሳሌ፤ አንድም ከጲላጦስ ወደ ሄሮድስ ከሄሮድስ ወደ ጲላጦስ እየተመላለሰ መከራ የመቀበሉ ምሳሌ፤ አንድም ከላይ ወደ ታች መፈተቱ የቃል ርደት፤ ከታች ወደ ላይ መፈተቱ የሥጋ ዕርገት፤ አንድም ከላይ ወደታች መፈተቱ ወደ መቃብር የመውረዱ፤ ከታች ወደ ላይ መፈተቱ ሞትን ድል አድርጎ የመነሣቱ ምሳሌ፤ ዙሪያውን ይፈትተዋል ሦስት ዓመት ከሦስት ወር ዞሮ የማስተማሩ ምሳሌ፤ ከሁለት ያነቃዋል ታቹን ግን አይለየውም ከሁለት ማንቃቱ የመለኮትና የትስብእት ታቹን አለመለየቱ የተዋሕዶ፤ አንድም ከሁለት ማንቃቱ የነፍስና የሥጋ ታቹን አለመለየቱ በዕለተ ዐርብ መለኮት ከነፍስም ከሥጋም ያለመለየቱ ምሳሌ፤ አንድም ከሦስት ያነቃዋል ታቹን አይለየውም፤ ከሦስት ማንቃቱ የሦስትነት አለመለየቱ የአንድነት ምሳሌ፤ አንድም የላዩን ወደ ታች የታቹን ወደ ላይ፣ የቀኙን ወደ ግራ፣ የግራውን ወደ ቀኝ ያደርገዋል፤ የላዩን ወደ ታች የቀኙን ወደ ግራ ማድረጉ ዲያብሎስ ከሹመቱ ከማዕረጉ የመዋረዱ፤ የታቹን ወደ ላይ የግራውን ወደ ቀኝ ማድረጉ በዲያብሎስ ቦታ አዳም የመግባቱ ምሳሌ፡፡ አንድም የላዩን ወደ ታች የቀኙን ወደ ግራ ማድረጉ አዳም ከክብሩ ከማዕረጉ የመዋረዱ፤ የታቹን ወደ ላይ የግራውን ወደ ቀኝ ማድረጉ አዳም በንስሐ ወደ ቀደመ ክብሩ ወደ ቀደመ ማዕረጉ የመመለሱ ምሳሌ፤ አንድም የላዩን ወደ ታች ማድረጉ የመለኮት ሰው መሆን ሰውነት፤ የታቹን ከላይ ማውጣቱ የሥጋን አምላክነትን ያስረዳል፡፡ አንድም የቀኙን ወደ ግራ ማድረጉ ኃያል መለኮት ደካማ ሥጋ፤ የግራውን ወደ ወደ ቀኝ ማድረጉ ደካማ ሥጋ ኃያል መለኮት ለመሆኑ ምሳሌ፤ በየቦታው ይመልሰዋል መመለሱ ከዕርገት በኋላ

---

[124] የማቴዎስ ወንጌል ፳፮ ፡ ፲፯

አንድ ሆኖ በአምላክነት ግብር ጸንቶ የመኖሩ ምሳሌ፤ ወኃደገ ንዴተ ሕላዌ ዘትካት ተመይጠ ወገብዐ ኀበ ስብሐቲሁ ወክብሩ እንዲል፡፡ አንድም የቀኙን ወደ ግራ ማድረጉ ዳግም ምጽአቱን፣ የግራውን ወደ ቀኝ ማድረጉ ነቢር በየማንን ያሳያል፤ ዐርገ ውስተ ሰማይ ወነበረ በየማነ እግዚአብሔር አቡሁ እንዲል፡፡[125] አንድም ከላይ ወደ ታች ማውረድ የጸሐፍት ፈሪሳውያን ተዋርዶ፤ ከታች ወደ ላይ ማውጣቱ የሐዋርያት ልዕልና አንድም የቀኙን ወደ ግራ ማድረጉ አይሁድ እንደወጡ የግራንውን ወደ ቀኝ ማድረጉ በአይሁድ ቦታ አሕዛብ እንደገቡ ለማጠየቅ እንከሰ ብዙርና ለነ ወአኮ ለአይሁድ እንዲል፡፡ በሀገራቸው አስበ ዲያቆኑን ቄሱ ይቀበለዋል፤ የጌታን መከራ መቀበል ይገባኛል ሲል ነው፤ በዚያ ያትመዋል ሕዝቡን የጌታን መከራ መቀበሉ ይገባችኋል ሲል፤ በሀገራችን ግን ዲያቆኑ ይቀበለዋል የእስጢፋኖስን መከራ መቀበል ይገባኛል ሲል በዚያ ያትመዋል ሕዝቡን የእስጢፋኖስን መከራ መቀበል ይገባችኋል ሲል ነው፡፡

እግዘኢብሔር ገባሬ ኵሉ፡፡

ኻያ ሁለቱን ሥነፍጥረት የፈጠረ እግዚአብሔር፤ ሙሴ በኦሪት ተርትሮ የተናገረውን አባ ሕርያቆስ እንደ ሸማ ጠቅሎ እንደ ወርቅ አንከብሎ ኵሉ በማለት ተናገረ፡፡

ወጣኔ ኵሉ

ሥራውን በቸርነት የጀመረ፤

ወፈጻሜ ኵሉ፡፡

ሥራውን በቸርነት የፈጸመ፤

አኃዜ ኵሉ፡፡

አንድም እግዚአብሔር ገባሬ ኵሉ የቸርነቱን ሥራ በኀሙስ ዕለት ወበመንፈቃ ለዕለት እትወለድ እምወለተ ወለትከ ብሎ የተናገረ፡፡ ወጣኔ ኵሉ የተአምራቱን ሥራ በማኅፀን የጀመረ፤ ወፈጻሜ ኵሉ የቤዛነቱን ሥራ በዕለተ ዐርብ የፈጸመ፤ አንድም ገባሬ ኵሉ ኦሪትን የሠራ፤ ወጣኔ ኵሉ ወንጌልን የሠራ፤ ወፈጻሜ ኵሉ እሱ የጀመረ እሱ የፈጸመ፤ አንድም ገባሬ ኵሉ ጥምቀትን የሠራ፣ ወጣኔ ኵሉ ንስሐን

---

125 ወደ ሰማይ ዐረገ በአባቱ በእግዚአብሔር አብ ዕሪናም ተቀመጠ፡፡ ማርቆስ ፲፮ ፡ ፲፱

የሠራ፤ ወፈጻሜ ኵሉ እሱ የጀመረ እሱ የፈጸመ። አንድም ገባሬ ኵሉ ዘጠኙን ዓለመ እሳት የፈጠረ፤ ወጣኔ ኵሉ ተጠምቆ ተጠመቁ የሚል፤ ወፈጻሜ ኵሉ ሥጋውን ደሙን ተቀብሎ ተቀበሉ የሚል፤ አጋዜ ኵሉ ሥጋውን ደሙን በመቀበል የሚያጸና፤ ወጸባጤ ኵሉ አልጠመቅም አልቀበልም በሚል ፍዳ የሚያመጣ።

ዘሎቱ ይሰግዱ መላእክት ወሊቃነ መላእክት መናብርት ወሥልጣናት አጋእዝት ወነይላት ፀሐይ ወወርኅ ወከዋክብት ወኵሉ ድርገታት።

ስመ ነገድ ነው፤ አንድም ስመ ማዕረግ ነው ሊቀ ጳጳስ፣ ጳጳስ፣ ኤጲስ ቆጶስ እንደ ማለት ነው። እሊህ ሁሉ አንድ ሆነው የሚሰግዱለት፤ ድርገት ወረዱ ማለት ምእመናን ሥጋ ወደሙን አንድ ሆነው ተቀበሉ ማለት ነው። አጻፋውን ለመላእክት የሰጡ እንደ ሆነ እለ ኢይብልዎሙ ዕገሌ ወዕገሌ ይላቸዋል፤ እለ ይወጽኡ እምውስተ መንበሩ ለአብ እንዲል ከእግረ መንበር እንደ አሸን ሲፈሉ የሚኖሩ ናቸው፤ ብዛታቸውን መናገር ነው። ለከዋክብት የሰጡ እንደ ሆነ እንደ ጋሻ ጉብጉብ እንደ ሾተል ጉጥ ተጠርቀው የሚኖሩ ልኩዓን ከዋክብት አሉ ብርሃን የሌላቸው ሰሌዳ ያላቸው ሕልመልመሌክ ምልክኤል ናርኤል ምልኤል የሚባሉ ዘመኑን ከዐራት ከፍለው የሚመግቡ ከዋክብት ናቸው። ዳግመኛም ዐሥራ ሁለት መገብተ አውራኅ ከዋክብት አሉ። እነዚህን ከመካከል አድርገው ሁለት መቶ አምሳ በፊት፣ ሁለት መቶ አምሳ በኂላ፣ ሁለት መቶ አምሳ በግራ፣ ሁለት መቶ አምሳ በቀኝ ሆነው ይሄዳሉና ድርገታት አለ።

እስመ እሙንቱ ቅኑያተ።

ፍጥረቶቹ ናቸውና አብኒ ቀነየ ኵሎ ዓለመ እንዲል።

ወምልክናሁ።

ግዛቱ።

ወግዝአቱ ለሞተ።

ርስቱ ጉልቱ ናቸውና። አንድም አንድ ወገን ተገዢዎቹ ናቸው።

Scanned by CamScanner

እንዘ ባዕል ውእቱ በኵሉ አንደየ ርእሶ እምኵሉ፡፡

በሁሉም ባለጠጋ ሆኖ ሳለ ከሁሉም ይልቅ ራሱን አዋረደ፤ አንደየ ርእሶ እንዘ ባእል ውእቱ ከመ አንትሙ ትብዐሉ በንዴተ ዚአሁ[126] እንዲል፡፡ አንድም ሁሉን የሚገዛ የባሕርይ ባለጠጋ ሲሆን ይህን ሁሉ ከመግዛት በአፍአ የነበረ ሥጋን ተዋሐደ፤ አንድም የማይራብ የማይጠማ መለኮት የሚራብ የሚጠማ ሥጋን ተዋሐደ፤ አንድም የማይደክም የማይታመም መለኮት የሚደክም የሚታመም ሥጋን ተዋሐደ፡፡

ፍቅር ሰሐቦ ለወልድ ኀያል እመንበሩ፡፡

የሰው ፍቅር ከክቡር ከልዑል ባሕርዩ ወደዚህ ዓለም አመጣው፡፡ አንድም የሰው ፍቅር ከብርሃናው ዓለም ወደ ጨለማው ዓለም ከሰፊው ዓለም ወደ ጠባቡ ዓለም ስቦ አመጣው፡፡ አንድም በቁሙ ከልዑል ዙፋኑ ጎትቶ አወረደው፡፡

ወአብጽሖ እስከ ለሞት፡፡

ለሞትም አደረሰው፤ አንድም ምን አደረገው ያልከኝን እንደሆነ ከዚህ ሁሉ ያደረሰው ማን ሆኖ ፍቅረ ደቂቀ ዕጓለ እመሕያው ነው እንጂ፡፡

ኦ ላህም ዘኢይትኄየል በቀርኑ ለእለ ይስሕብዎ፡፡

ሲስቡት ሲጎትቱት በቀንዱ የማይበረታታ ላህም ምን ይረቅ ምን ይደንቅ ኦ ወዮ! እንደምን ያለ ረቂቅ ነው ለዚህ አንክሮ ይገባል፡፡

ወያጸንን ክሣዶ ለእለ ይጠብሕዎ፡፡

ሲያርዱት ሲያወራርዱት አንገቱን ዘንበል አድርጎ የሚሰጥ ላህም እንደምን ያለ ነው? አንድም ሲስቡት ሲጎትቱት በቀንዱ የማይበረታታ ላህም ወልደ እግዚአብሔር ምን ይረቅ ምን ይደንቅ ኦ ወዮ! እንደምን ያለ ረቂቅ ነው ለዚህ አንክሮ ይገባል፡፡

ኦ በግዕ ዘኢይነብብ በቅድመ ዘይቀርፆ፡፡

ጸጉሩን ሲሸልቱት ከመዐልት ሐሩር ከሌሊት ቁር የምድንበትን ብሎ የማይናገር በግዕ እንደምን ያለ ነው? አንድም መከራ በሚያጸኑበት ፊት በምን ዕዳዬ ነው የምትገድሉኝ ብሎ የማይናገር በግዕ ወልደ

---

126 የባሕርይ ባለጠጋ ሲሆን ራሱን ድሀ አደረገ፤ በእሱ ድህነት እናንተ ትከብሩ ዘንድ፡፡ ፩ኛ ቆሮንቶስ ፰ ፡ ፱

እግዚአብሔር ምን ይረቅ ምን ይደንቅ አ ወዮ! እንደምን ያለ ረቂቅ ነው ለዚህ አንክሮ ይገባል።

አ ትዕግሥት ዘአስሠተ አፉሁ በሕማሙ በቅድመ አለ ይረግዝዎ።

ሲወጉት ሲቸነክሩት የማይናገር ትዕግሥት ወልደ እግዚአብሔር እንደምን ያለ ነው አ ወዮ ለዚህ አንክሮ ይገባል። አንድም ትዕግሥቱ ለወልደ እግዚአብሔር የወልደ እግዚአብሔር ትዕግሥቱ እንደምን ያለ ነው? አንድም አስቀድሞ ማያትን አፍስሼ ነፋሳትን አንፍሼ ብርሃናትን አመላልሼ በጋና ክረምትን መዐልትና ሌሊትን አፈራርቄ፤ በዝናም አብቅዬ በፀሐይ አብስዬ መገብኳችሁ፤ አሁን ደግሞ ላድናችሁ ብመጣ የምትሰቅሉኝ የምትገርፉኝ በምን ዕዳዬ ነው? አላለምና ትዕግሥቱ እንደምን ያለ ነው። ከዚያ አጣሊሰ ኢኮና ተናጋሬ አላ ዘዚአነ ይላል ከዚህ እንዲህ አለ እንደ ምን ነው ቢሉ ከዚያ አስተሥርይነቱን ከዚህ ትዕግሥቱን መናገር ነው፤ እለ ይረግዝዎ አለ የወጋውማ አንድ ጭፍራ አይደለም ቢሉ መጽሐፍ ስም ካልጠራ ማብዛት ልማድ ነው በተአምኖ አመ ነገርዎ ለኖኅ ብዕዕት አንተ እንተ ተአምኒ ከመ ይከውን ቃል ዘነገሩኪ እምኀበ እግዚአብሔር እንዲል አንድም በቀኖት የቸነከሩትን በአክሊለ ሦክ የወገትን ቆጥሮ፤ አንድም ሺ መከር አንድ ወረወር እንዲሉ ፈቃድ የሁሉም ነውና።

አ ኅብስት ዘወዕአ እመዝገብ ዘተሣየጠ ዮሴፍ።

መሶብ ሲል ነው፤ ከመሶበ ወርቅ የተገኘ ኅብስት ምን ይረቅ ምን ይደንቅ አ ወዮ! እንደምን ያለ ረቂቅ ነው ለዚህ አንክሮ ይገባል። አንድም በቁመ እመዝገብከ የምሥጢር መዝገብ ከተባለች ከእመቤታች የተገኘ ኅብስት እንደምን ያለ ነው፤

ወረከበ በውስቱታ ባሕርየ ዕንቁ ክቡረ።

በውስጧም ክቡር ዕንቍን ያገኘባት፤

አ ጽዋዕ ዘወዕአ እምጽርሐ ዘአቦአ ውስቱታ ብእሲ።

ሰው ካልገባበት አዳራሽ የተገኘ መጠጥ ምን ይረቅ ምን ይደንቅ አ ወዮ! እንደምን ያለ ረቂቅ ነው ለዚህ አንክሮ ይገባል። አንድም ዘርአ ብእሲ ከሌለባት ልማደ አንስት ካላገኛት ከእመቤታችን ለተወለደ ጌታ አንክሮ ይገባል። በሀገራቸው ሁሉ ይሸጣል ዋጋውን ጽፎ ይተወዋል

ያን አይቶ የሚቻለው ከሆነ ገዝቶ ይሄዳል፤ የማይቻለው ከሆነ ከፍቶ ገብቶ አይቶ ዝም ብሎ ይሄዳል፡፡ ዮሴፍም ያን አይቶ ከፍቶ ቢያይ መብሉ መጠጡ ተዘጋጅቶ አግኝቶታል ይህንም በዚያ ግሥ ተናገረ፡፡

ኦ ዝንቱ ትእምርተ መስቀል ዘተፈልጠ እምዝንቱ ኅብስት እንዘ ኢኮነ ፍሉጠ ወኢብዑደ፡፡

ከዚህ ኅብስት ሳይለይ የተለየ ይህ ትእምርተ መስቀል ምን ይረቅ ምን ይደንቅ ኦ ወዮ! እንደምን ያለ ረቂቅ ነው ለዚህ አንክሮ ይገባል፡፡

አላ አርአያሁ ወጣዕሙ ልምላሜሁ አሐዱ ውእቱ፡፡

መልኩ መዓዛው ጣዕሙ ልዝብነቱ አንድ ነው እንጂ፡፡

በከመ ኢኮነ ፍሉጠ ወኢብዑደ ዝንቱ ትእምርተ መስቀል እምዝንቱ ኅብስት፡፡

መለኮቱ ከትስብእቱ ትስብእቱ ከመለኮቱ እንዳልተለየ፤ ይህም ትእምርተ መስቀል ከኅብስቱ አልተለየም፤

ወከማሁ ይደመር ዕበይከ በትሕትናነ ወትሕትናነ በዕበይከ፡፡

እንደዚሁ ሁሉ ልዑል ባሕርይህ ከትሑት ባሕርያችን ትሑት ባሕርያችን ከልዑል ባሕርይህ ጋር አንድ ይሁን፡፡

አንተ አኃዜ ዓለም እግዚአብሔር አምላክነ፡፡

ዓለሙን የፈጠርህ ፈጣሪያችን እግዚአብሔር አንተ ነህ፤ ወፈጠረ እሥራ አየራተ ይላል ኻያ ዓለማትን ፈጥሯል፡፡ እነዚህም ዘጠኝ ዓለመ እሳት፣ አምስት ዓለመ መሬት፣ ዘጠኝ ዓለመ ማይ፣ ሁለት ዓለመ ነፋስ፣ ዘጠኙ ዓለመ እሳት የሚባሉት ሰባቱ ሰማያት፣ አንዱ በዚህ ዓለም ያለው፣ አንዱ በመሠረተ ምድር ያለው ነው፡፡ አምስቱ ዓለመ መሬት የሚባሉት ብሔረ ሕያዋን፣ ብሔረ ብፁዓን፣ ገነት፣ በርባሮስ፣ ይህ ዓለም ናቸው፡፡ አራቱ ዓለመ ማይ የሚባሉት ሐኖስ፣ ጠፈር፣ ውቅያኖስ፣ በዚህ ዓለም ያለው ይህስ ለተልእኮ የመጣ ነው አይቆጠርም ብሎ በመሠረተ ምድር ያለው፡፡ ሁለቱ ዓለመ ነፋስ የሚባሉት አንዱ ሐኖስን የሚያነዋወጽ ነው ባቢል ይባላል፤ አንዱ በዚህ ዓለም ያለው ይህስ ለተልእኮ የመጣ ነው አይቆጠርም ብሎ በመሠረተ ምድር ያለው ነው፡፡

ይ.ዲ. ጸልዩ፡፡

ዲያቆኑ ጸልዩ ይበል፡፡

ይ.ሕ. አቡነ ዘበሰማያት።

ሕዝቡም በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ እያሉ ይጸልዩ።

ይ.ካ.

ይበል ካህን።

ንስማዕ እንከ ዘንተ ቃለ እስከ ነፍስ ደኃሪት።

እስከ ቃል ሕቅታ ይላል እስከ ዕለተ ሞት ይህንን ቃል እንስማ፤ የሚቻለው አውራ ጣቱን ይዞ የማይቻለው አንገቱን ዘንበል አድርጎ ይህን ቃል መስማት ማስቀደስ ይገባል። አንድም እስከ እስትንፋስ ደኃሪት ይላል እስከ ነፍስ ሕቅታ ድረስ ይህንን ቃል እንስማ፤ ይትወላወል ሰብእ እምጊዜ ልደቱ እስከ ዕለተ ሞቱ እንዲል ሰው ከተወለደ ጀምሮ እስከ ዕለተ ሞቱ ድረስ ሲያወጣ ሲያወርድ ይኖራል የመጨረሻ ቁርጥ ያለ ነገር የሚናገረው በጊዜ ሞቱ ነውና።

በዘባቱ ንሰክይ።

በምንከሰስበት ገንዘብ የምንከሰስበትን እንዳንከሰስ፤

ወበዘባቱ ንትኴነን።

በሚፈረድብን ገንዘብ የሚፈረድብንን እንዳይፈረድብን፤

ወበዘባቱ ንትመሐር።

ይቅር በሚለን ገንዘብ ይቅር ይለን ዘንድ ይህንን ቃል እንስማ።

በከመ መጽአ ወልድ እምሰማየ ሰማያት ለኵንኖ ወለምሕረት።

እግዚአብሔር ወልድ በጎጥአን ሊፈርድባቸው ለጻድቃን ሊፈርድላቸው እንደመጣ ይቅር ይለን ዘንድ ዛሬ ይቅር የምንባልበትን ይህንን ቃል እንስማ።

ወከማሁ ዝንቱ ጎብስት።

ይህም ጎብስት፤

መስክይ ውእቱ።

የሚከስ የሚወቅስ ነው።

ወመኰንን ውእቱ።

የሚፈርድ የሚኰንን ነው።

Scanned by CamScanner

ወመሓሪ ውእቱ::

ይቅር ባይ ነው::

እምዝንቱ መደንግፅ ትፍራህ ነፍስ::

ከሚያስደነግጥ ከዚህ ቃል የተነሣ ነፍስ ትፍራ፤

ወይርዐድ መለያልይ::

የሰውነት ሕዋስ ሁሉ ይራድ ይንቀጥቀጥ::

ወይሰበር አናቅጸ ልብ ዘውስጥ::

ውሳጣዊ ልቡና ይሰባበር፤ አንድም ኢአማኒ ልቡና ይመን ጥሩጥሩን ይተው::

ለእንስሳት ለአራዊት ለዕፀዋት ለአዕባን አንድ፣ ለሰው ሁለት ጠባቂ መልአክ አለው:: የሌሊቱ ሲሄድ የመዐልቱ ሲመጣ ይገናኛሉ፤ እንደምን ሆነህ አደርህ ይለዋል፤ ክፉ ሰው የሆነ እንደ ሆነ እጁ ከመግደል ቃሉ ከመበደል ሰውነቱ ከኃጢአት ከክፋት ልቡናው ከትዕቢት አንደበቱ ከሐሜት ያልተለየ ክፉ ሰው አግኝቼ በመከራ አደርኩ ሂድ አንተም ታገኘዋለህ ይለዋል፤ እያዘነ ይመጣል፤ ደግ ሰው የሆን እንደ ሆነ እጁ ከምጽዋት አንደበቱ ከጸሎት ሰውነቱ ከንጽሕና ልቡናው ከትሕትና ያልተለየ ደግ ሰው አግኝቼ በተድላ በደስታ አደርኩ ታገኘዋለህ ይለዋል፤ ደስ እያለው መጥቶ ቀርቦ ይጠብቀዋል፤ ክፉ ሰው የሆነ እንደሆነ ይህን ገለህ እንስሳት አራዊትን ብታስጠብቀን ይሻለን ነበር እያሉ ይጸልዩበታል፤ ደግ ሰው የሆነ እንደሆነ ይህን ገለኸብን ምን ታስጠብቀን ይሆን እያሉ ዕድሜ እንዲሰጠው ይጸልዩለታል፤ ውሎ ውሎ ከቤት፣ ኖሮ ኖሮ ከመሬት እንዲሉ ምንም በጎ ቢሠሩ ሞት አይቀርምና በሚሞትበትም ጊዜ ወስደው ቀረብ አድርገው ያቆሟታል፤ ዛሬ ሥጋውን ደሙን የሚቀበል ሰው ቀረብ ብሎ እንደሚቆም:: ያችም ነፍስ ቀረብ ብላ ትሰግዳለች ወታቀድም ሰጊደ ለስብሐተ ልዑል ወትገብዕ ነፍስ ኀበ ዘወሀባ ቀዲሙእንዲል::[127] በእዚህ ጊዜ ሲጠብቋት የነበሩት መላእክት ኦ እግዚኦ ዕሥያ ለዛቲ ነፍስ አቤቱ ይህችን ነፍስ ካስጠበቅኸን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ጽድቅ እንጂ ኃጢአት ደግነት

127 የሞት ነገር እንዲህ ነው ከልዑል ዘንድ የትዕዛዝ ቃል ከመጣ በኋላ እገሌ ይሙት ባለ ጊዜ ነፍሱ ከሥጋው ትለያለች፤ ዳግመኛም ወደ ሰጣት ትመለሳለች ለልዑል ጌትነትም አስቀድማ ትሰግዳለች:: ዕዝራ ሱቱኤል ፮ ፡ ፰

እንጂ ክፋት ሠርታ አታውቅምና መንግሥተ ሰማያት እንጂ ገሃነመ እሳት አይገባትም ነገር ግን አንተ ባወቅህ ብለው ይመሰክሩላታል፤ ሰባት ቀን መንግሥተ ሰማያትን ሰባት ቀን ገሃነመ እሳትን አዙራችሁ አሳይታችሁ ወስዳችሁ በገነት አኑሯት ኋላ ነፍሷን ከሥጋዋ አዋሕጂ መንግሥተ ሰማያትን እስካወርሳት ድረስ ይላቸዋል፤ እነሱም ክፉ ብትሠሪ ኖሮ ከዚህ ትገቢ ነበር ብለው ገሃነመ እሳትን ያሳይዋታል፤ ነገር ግን በጎ ሥራ ሠርተሻልና ኋላ ከዚህ ትኖሪያለሽ ብለው መንግሥተ ሰማያትን አዙረው አሳይተው በገነት ያኖሯታል። ወየዐውድዋ ለነፍስ ሰቡዐ መዋዕለ ወያርእይዋ ሰብዐተ ሥርዓታተ እንዲል። ክፉ ሰው የሆነ እንደ ሆነ ወስደው አርቀው ያቆሟታል ዛሬ ሥጋውን ደሙን የማይቀበል ሰው ርቆ እንደሚቆም፤ አ እግዚኦ ኩንና ለዛቲ ነፍስ አቡቱ ይህችን ነፍስ ካስበጠቅኸን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ኃጢአት እንጂ ጽድቅ፣ ክፋት እንጂ ደግነት ሠርታ አታውቅምና ገሃነመ እሳት እንጂ መንግሥተ ሰማያት አይገባትም፤ ነገር ግን አንተ ባወቅህ ይሉታል፤ ሰባት ቀን መንግሥተ ሰማያትን ሰባት ቀን ገሃነመ እሳትን አዙራችሁ አሳይታችሁ ወስዳችሁ በሲኦል አኑሯት፤ ኋላ ነፍሷን ከሥጋዋ አዋሕጂ ገሃነመ እሳት እስካወርዳት ድረስ ይላቸዋል፤ እነሱም ደግ ሥራ ብትሠሪ ኖሮ ከዚህ ትገቢ ነበር ብለው መንግሥተ ሰማያትን ያሳይዋታል፤ ነገር ግን ክፉ ሥራ ሠርተሻልና ኋላ ከዚህ ትኖሪያለሽ ብለው ገሃነመ እሳትን አዙረው አሳይተው ወደ ሲኦል ያወርዷታል። ወየዐውድዋ ለነፍስ ሰቡዐ መዋዕለ ወያርእይዋ ሰብዐተ ሥርዓታተ[128] እንዲል። መስክይ፤ ወመኰንን፤ ወመሓሪ አለ የጧት የማታ ጸሎት ከቤተ እግዚአብሔር ይሁን ብለዋል። ስድስት መቶ የሌሊት ስድስት መቶ የመዐልት ጠባቂ መላእክት አሏት ታቦት፣ ሥዕል፣ መስቀል ካለበት ጥግ ይዞ ለመዋጋት።።

ናሁ ተፈተተ ገዝኑ ኅብስት መለኮታዊ ዘይነሥእ።።

እነሆ መለኮት የተዋሐደው ነፍስ የተለየው ቅዱስ ሥጋው ክቡር ደሙ እነሆ ተዘጋጅቷል የሚቀበል ይምጣ።።

128 እነዚያ የኃጥአንነፍሳት ይዞራሉ እንጂ ወደ ጻድቃን ማደሪያ አይገቡም ከዚህ በኋላ መከራ ይቀበላሉ ይጨነቃሉ ያዝናሉም ሰባቱንም ሥርዓታት ያሳዩአቸዋል። ዕዝራ ሱትኤል ፮ ፥ ፱

መቅድመ ሕቱ ርእሰክሙ።

ሥጋወ ደሙን ከመቀበል አስቀድማችሁ ሰውነታችሁን መርምሩ፤ መመርመር ከልቡና፣ ከመጻሕፍት፣ ከመምህራን ነው።

ወአንጹሑ ነፍስተክሙ።

ሰውነታችሁን ከኃጢአት ከክህደት ንጹሕ አድርጉ

እመቦ ዘኢኮነ ንጹሐ ይትገኃሥ።

ከኃጢአት ንጹሕ ያልሆነ ሰው ቢኖር ይከልከል።

ወእመቦ ዘወድቀ በኀጢአት ኢይርሳዕ።

በኃጢአት የተሰነካከለ ሰው ቢኖር ኃጢአቱን አይዘንጋ፤

እስመ ዘኢይትረሳዕ።

ኃጢአቱን የማይዘነጋ በክብር አይረሳም፤ ኃጢአቱን የሚዘነጋ ግን በክብር ይረሳል። አንድም ዛሬ ኃጢአቱን የማይዘነጋበገሃነም አይረሳም፤ ዛሬ ኃጢአቱን የሚዘነጋ በገሃነም ይረሳል።

ወለእመቦ ዘያስተቃልል ዘንተ ሙርባነ።

ይህን ሥጋውን ደሙን የሚንቅ የሚያቃልል ሰው ቢኖር አይቁረብ፤

ኢይቁም አላ ይትከላእ።

ይከልከል እንጂ አይቅረብ።

አኮ በከ በከመ ትሬእይዎ ለዝንቱ ኅብስት በከመ ኅብስት ምድራዊ።

በመልክዐ ኅብስት የምታዩት ይህ ኅብስት እንደ ምድራዊ ኅብስት ብላሽ ተራ አይደለም። አንድም አኮ በከ ዘከመ ትሬእዩ ይላል ሳይለወጥ ተራ ብላሽ ሆኖ እንደ ምታዩት እንደ ምድራዊ ኅብስት ያልተለወጠ አይደለም።

አላ እሳተ መለኮት ውእቱ።

ተለውጦ የአምላክ ሥጋ የአምላክ ደም ነው እንጂ።

አይ አፍ ዘይትፈዐም ዘንተ ኅብስተ።

እሳተ መለኮት ብሎ ነበርና ይህን ኅብስት መቀበል የሚቻለው አፍ እንደ ምን ያለ ነው።

Scanned by CamScanner

ወአይ አስናን ዘየሐይክ ዘንተ ኅብስተ፡፡

ዕብነ አድማስ ብሎ ነበርና ይህን ኅብስት ማላመጥ የሚቻለው ጥርስ እንደምን ያለ ነው፡፡

ወአይ ከርሥ ዘያገምር ዘንተ ኅብስተ፡፡

ግሩም ውእቱ ዘኢይደፈር ብሎ ነበርና ይህን ኅብስት መወሰን የሚቻለው ሆድ እንደምን ያለ ነው፡፡

ወይእዜኒ ንበል በከመ ምሕረትከ፡፡

አቤቱ ፈጣሪያችን ኀጢአታችንን ይቅር ማለትህ እንደ ይቅርታህ እንደ ቸርነትህ ነው እንጂ፡፡

ወአኮ በከመ አበሳነ፡፡

እንደ ኀጢአታችን ብዛት እንደ ሰውነታችን ክፋት ባልተገባንም ነበር፡፡ ያልጠፋንው ከእግዚአብሔር ምሕረት የተነሣ ነው እንዳለ ኤርምያስ፡፡ አንድም ሥጋህን ደምህን መስጠትህ እንዳንተ ቸርነት ነው እንጂ እንደ እኛ ኀጢአት ባልተገባን ነበር፤ አንድም መቅሠፍቱን ቅሉ ማምጣትህ እንደ ቸርነትህ ነው እንጂ እንደ እኛ ኀጢአት አይደለም እንደ እኛ ኀጢአትስ ፈጥኖ በዝቶ በተደረገብን ነበር፡፡ አንድም በጸናብን ነበር፡፡ ሦስት ጊዜ በከመ ምሕረትከ ማለቱ የሦስትነት ቃሉ ያለመለወጡ የአንድነት ምሳሌ፡፡ አንድም በሦስት ወገን በኀልዮ፣ በነቢብ፣ በገቢር የሠራንውን ኀጢአት ይቅር በል ለማለት፡፡ ይህን የተናገረው ፈያታዊ ዘየማን ነው ተዘከረነ እግዚኦ በውስተ መንግሥትከ ባለ ጊዜ አያይዞ ተናግሮታል፡፡

ሠራዊተ መላእክቲሁ ለመድኃኔ ዓለም ይቀውሙ ቅድሜሁ ለመድኃኔ ዓለም፡፡

የመድኃኔ ዓለም አገልጋዮች ሠራዊተ መላእክት ከፊቱ ይቆማሉ፤ አንድም ከፊቱ ቆመው ያመሰግናሉ፡፡

ወይኬልልዎ ለመድኃኔ ዓለም ሥጋሁ ወደሙ ለመድኃኔ ዓለም፡፡

መላእክት የሚጋርዱት የሚያመሰግኑት የመድኃኔ ዓለም ሥጋውና ደሙ ይህ ነው እያሉ ከፊቱ ቆመው ያመሰግናሉ፡፡ ሥጋወ ደሙ ከሚፈተትበት ስሙ ከሚጠራበት ከቤተ ክርስቲያን መላእክት አይለዩም፡፡ በመዐልት ስድስት መቶ በሌሊት ስድስት መቶ

ይጠብቋታል። በቅዳሴ ጊዜ ግን እንደ ሻሽ ይነጠፋሉ እንደ ግንድ ይረበረባሉ እንደ ቅጠል ይረግፋሉ።

ወንብጻሕ ቅድመ ገጹ ለመድኃኔ ዓለም።

መላእክት ከፊቱ ቆመው እንዲያመሰግኑት እኛም ከፊቱ ቆመን እናመሰግነው ዘንድ በባለሟልነት ለመቆም ወደ እርሱ እንቅረብ።

በአሚነ ዚአሁ ለክርስቶስ ንገኒ።

እሱን በማመን ጸንተን በጸሎት በአምልኮት ለክርስቶስ እንገዛለን። ይህን ሠራዊት ንፍቅ ቂስ ንፍቅ ዲያቆን ከመንጦላዕት በአፍአ ሆነው፤ ሠራዒው ቂስ፣ ሠራዒው ዲያቆን፣ አብሪ ቂስ በመንጦላዕት ውስጥ ሆነው እየተቀባበሉ ይበሉ፤ በአፍአ ያሉት የነቢያት፣ በውስጥ ያሉት የሐዋርያት ምሳሌ ነው። በአሚነ ዚአሃ ለማርያም ንገኒ ብሎ የጨመረ ቅዱስ ያሬድ ነው።

ይ.ዳ. ንፍቅ እንዘ ይበውእ አርኅዉ ኖኅተ መካንንት።

አናጉንስጢሳውያን ደጁን ክፈቱ ይበል።መዓርገ ቤተ ክርስቲያንን ሲመስል በመካንንት መስሏቸው ነበረና በምሳሌያቸው መካንንት አላቸው። መክፈቱ ግን ጌታን ሁሉም እንዲያየው ብለው በገበያ ቀን በአደባባይ ሰቅለውታልና የዚያ ምሳሌ፤ አንድም ንጉሥ ሲፈርድ እንደማይሠወር ጌታም በዳግም ምጽአት በግልጥ የመፍረዱ ምሳሌ። አንድም ከእርሱ የሚሠወር ፍጥረት የለምና፤ ወአልቦ ዘተፈጥረ ዘኢኮነ ክሡተ በቅሜሁ ወሥጉሉ ክሡት ወስጡሕ በቅድመ አዕይንቲሁእንዲል።[129]

ይ.ዳ. እለ ትቀውሙ አትሕቱ ርእሰክሙ።

ዲያቆን በቅዳሴ ጊዜ የቆማችሁ ራሳችሁን ዘንበል ዘንበል አድርጉ፤ አንድም ርእሰ ልቡናችሁን በትሕትና ክሣደ ልቡናችሁን በንስሐ ዝቅ ዝቅ አድርጉ ይበል። አንድም ልቡናችሁን ከትዕቢት አዋርዱ በል።

ስግዱ ለእግዚአብሔር በፍርሃት።

ዲያቆን በፈሪሃ እግዚአብሔር ሆናችሁ ውደቁ ይበል፤ ጸሎተ ንስሐ የሚያገመው አሰግዶ ነውና።

---

[129]የተፈጠረ፤ በፊቱ ያልተገለጠ የለም ሁሉም በፊቱ የተገለጠ ነው እንጂ። ዕብራውያን ፬ ፥ ፲፫

ቅዳሴ ማርያም ጉባዔ ዐሥራ ሦስት::

ይ.ሕ. ቅድሜከ እግዚኦ ንሰግድ ወንሴብሐከ::

አቤቱ በፊትህ ወድቀን እናመሰግንሃለን፤ አንድም እያመሰገንህ በፊትህ እንወድቃለን ይበሉ::